# የትዝብት ዕይታ

# ችንፈት ሲሉ ድል ስንል

በብሔራዊ ራዕይ ላይ የተመሠረተና ሕዝባዊ ዓላማ ይዘው በአንድ ሀገር የፖለቲካ ድርጅት ስር የሚታገሉ አባላት፥ መቸነፍንና ማቸነፍን፥ ድል ማድረግንና ድል፥መነሳትን፥ የሚገመግሙት፥ ከዓላማቸው ህያውነትና ህይወት አልባነት፥ ከሕዝብ ተቀባይነት ወይም ተቀባይነት ማጣት፥ በችግር ጊዜ አይበገሬ መሆን ወይም መፍረክረክ እና ከመሳሰሉት አንፃር ብቻ አይደለም።

ለእነርሱ፥ የችንፈት ትርጉሙ፥ ክብርን ሸጦ፥ የቆሙበትን የትግል ቃልኪዳን ረስቶ፥ ለአምባገነኖች ተንበርክኮ፥ የሀገራቸውንና የሕዝባቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለከንቱ ሥልጣን ለውጦ፥ በድርጅት መሠረታዊና ዘላቂ ዓላማና ግብ ተደራድሮ፥ የተሰውቱን ጓዶቹን አፅም አዋርዶና እራሱም ተዋርዶ ፥ ተስፋውንና ራዕዩን አጨልሞ የከንቱ ከንቱ ሆኖ መቅረትን ነው። በብርቱ ፅናት ለመታገል ከሚያስችላቸው ዓይነተኛ ዓብነት አንዱ፥ የትግሉ ዓላማ ትክክለኛ መሆን አለመሆን ነው። ትክክልኛና ፍትኃዊ ዓላማ ይገኘ ነው የምታገለው ብሎ ለሚል ታጋይ፥ የትግሉ ዓላማ፥ ለቀራጡ ታጋይ ትውልድ ሕይወት ወሳኝነት አለው ማለት የሚቻል ይመስለናል።

ፀረ ሕዝብ ኃይላት በወቅታዊ ሁኔታ በመታገዝ የሚያገኙት አንፃራዊ የበላይነት ምንም ጊዜም ቢሆን፥ በፅኑ ዓላማ ላይ በተመሠረተ ትግል ለሚዋደቅ ታጋይና አይበገሬ ኃይል ከመጤፍ የሚቆጠር አይደለም። ያማ ቢሆን ኖሮ በወቅቱ ከዓለም ኃያልን መካከል አንዷ የነበረችው ፋሽስት ኢጣሊያ በ1933 ዓም ማይጨው ላይ የኢትዮጵያን ጦር በመርዝና በጋዝ ጭስ ጨፍጭፋ ዋና ከተማችን በያዘች ጊዜ፥ ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትጥቁን በመፍታት ለቅኝ ገዥዎች ተንበርክኮ በተገዛ ነበር። ያንን ግን አላደረገውም። አልሞከረውምም። ምንም እንኳን በወቅቱ የነበሩት መሪዎቹ ለውጭ ወራሪ ኃይል ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን አጋፍጠው ቢሰወሩም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የየራሱን የጎብዝ አለቃና ያርበኞች መሪዎች እየመረጠ በዱር በገደሉ፥ በጫካና ሸንተረሩ እየተዋደቀ ሀገሩን ከኢጣሊያ ፋሽስት ወራሪ ኃይል ነፃ በማውጣት ክብሩን፥ ታሪኩንና ማንነቱን አስከብሯል።

ሌላም ተመሳሳይ ተጨማሪ የታሪክ ማገናዘቢያ ካስፈለገም፥ በ1982 ዓም በወያኔና በደርግ የተደገመውን አሳፋሪ የታሪክ ክስተት ማንሳት ይቻላል። ድርጊቱ የቅርብ ትዝታ በመሆኑ ወደ ዝርዝር መግባቱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም። በዕርግጠኝነትና ያለ አንዳች ውዳሴ ከንቱ መነገር የሚገባው ግን ፥ የገባበትን ሕዝባዊ ቃልኪዳን ሳያጥፍ ወያኔን በመፋለም ላይ ያለው አይበገሬው ዕውነተኛው የኢሕአፓ ታጋይ ኃይል፥ ከቀደምቱ አርበኛ ትውልድ የወረሰውን አኩሪ ታሪክ አንግቦ እስከ መጨረሻው የትግል ምዕራፍ እየተዋደቀ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ማብቃትን ነው። ይህንን ከማድረግ ደግሞ የሚያግደው ምድራዊ ኃይል አይኖርም። ችንፈት የሚባል ቃል የኢሕአፓን ታጋይ ሲያለፍም አይነካው!

ሦስት ተፈራራቂ ፀረ ሕዝብ የሆኑትን አምባገነን ሥርዓት አይከፍሉ መሥዋዕት በመክፈል ማንነቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በደሙና በአፅሙ ያስመሰከረ ጀግና አብዮታዊ ትውልድ፥ በወቅታዊው የፖለቲካ ሂደት በሚከሰቱ ተለዋዋጭ ውጣ ወረዶች፥ የኃይል ሚዛን አሰላለፎች፥ ያቋም መንሸራሸሮች፥ የየግለሰቦች ድክመቶችና የትግሉ ሂደት ርዝማኔዎች ምክንያት፥ በትግሉ ዕምነትና ፅናት ላይ የችንፈት ምልክቶች ከቶ ሊያሳይ አይችልም። አይገባውምም። ቀድሞዉኑ ትግል ሲጀመር፥ ከጥንት ከጧቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ቃል ኪዳን ሲገባ፥ የተሰውቱን ጓዶች መሥዋዕታዊ አደራ በመቀበልና በትግሉ መቀጠል ሲታመን፥ አኩሪ የሆነውን የሀገር ታሪክና ባህል ሲያስከብር እየታገለ

ለቆየና አሁንም እስከ መጨረሻው ድረስ ለመታገል ቆርጦ ለተነሳ ኃይል፥ መቸነፍ የሚባልን ቃል በእርሱ መዝገበ- ቃላት ውስጥ ቢፈልገውም እንኳን አይገኘውም።-

እንዲህ ከመቅጽበት ከሚለዋወጠው የሀገራችን የፖለቲካ ውሽንፍር ሂደት ባሻገር፥ ሌሎች የተጠበቁና ያልተጠበቁ ክስተቶች ወደ ፖለቲካው መድረክ ብቅ ማለታቸው አይቀሬ ነው። ከዚህም በቀር፥ የአካባቢና የዓለም-አቀፍ ሁለንተናዊ ክስተቶች በሀገራችን የፖለቲካ መልካ ምድር ውስጥ የተለያዩ ይዘት ያላቸው ተፅንዖች መምጣታቸው የሚያከራክር አይደለም። እነዚህ ተፅንዖች፥ ተወደደም ተጠላ፥ በትግሉ ባኅርይና ይዘት ላይ የሚያደርጉት ግፊትና አስተጋብዖ በቀላሉ የሚገመት አይሆንም። በተለይም ዛሬ በአንድ ልዕለ-ኃያል ቁጥጥር ስር በምትዋኸቀው ዓላማችን ይህ ነው የማይባል አሉታዊ ብቻ ሳይሆን ጎጅ የሆኑ ውጤቶችን ማሳደራቸው የሚካድ ሊሆን አይችልም ። አብሶማ የሦስተኛው ዓለም ተብሎ በሚጠራው በአፍሪካ፥ በእስያና በደቡብ አሜሪካ በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ የሚያመጡት ቀጥታና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጎዳቶች ተዘርዝረው የሚያልቁ አልሆኑም። ይህ ሀቅ በሀገራችን በኢትዮጵያ ላይ ያስከተለውን የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ቀውስ፥ መጠኑና ስፋቱ፥ ጉዳት ከደረሰበት ከራሱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በስተቀር፥ ሌላ በትክክል የሚረዳው አይኖርም።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰቆቃና ጉዳት ከሌሎች ሀገሮች የተለየ ከባድና አንገፍጋፊ የሚያደርገው፥ በሥልጣን ላይ ያለው ብሄረተኛ ቡድን፥ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ለባዕዳን አሳልፎ መስጠቱና ሀገራችንንም የዓለም ሕዝቦች መሳቂያ መሳለቂያ መድረጉ ነው። ይህ ሀቅ ደግሞ ተቃዋሚ ድርጅቶች ነን በሚሉ ኃይሎች ዘንድ ሁለት የተለያዩ አመለካከቶችን ሊያስከትል ችሏል። አንደኛው ክፍል፥ ወያኔ በሁለንተናዊ መልኩ ጠንካራ ነው፥ የዓለም አቀፍ ሁኔታ ለመለስ ዜናዊ አመች ሆኖለታል። ምዕራባውያን ያልተቋረጠ ድጋፍና ትብብር እየለገሱት ናቸው። የአካባቢያችን ይዞታ ለትግል አያመችም። ስለሆነም እየተገዙ መታገል የወቅቱ የትግል ስልታችን መሆን ይገባዋል ከሚል ነው። መቸነፋችንን አምነን ተቀብለን፥ወያኔ የሚሰጠንን የፖለቲካ መንቀሳቀሻ ዕድል መጠቀም የዘመኑ የፖለቲካ ፈሊጥ ልናደርገው የግድ ይላል ብለው፥ ለመቸነፋቸው ማጠየቂያ በማግኘት ብቻ ረክተው የተቀመጡና ወያኔ የቸረላቸውን ፍርፋሬ ለመጠቀም በከንቱ ተስፋ የሚያቋምጡ ናቸው። እየተገዙ ለሚታገሉና በወያኔ ህገወጥና ዘረኛ ሥርዓት ላይ የተመሠረተውን ህግ መንግሥት አምነው ለተቀበሉ ደግሞ፥ የወያኔ አዳራሽ ክፍት ነው። በነ መለስ ዜናዊ ጓይላ ካጨበጨቡም፥ ለተወሰነም ጊዜም ቢሆን ዕድሜ ይኖራቸዋል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ክብርና ተዓመኔታን ግን እስከ-ወዲያኛው ድረስ አያገኙትም።

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ፥ በአንደኛው ክፍል ከተዘረዘሩት ምክንያቶችና መነሻ የተለየና የተፃረረ ድምዳሜ የደረሱ የተቃዋሚ ኃይሎች ናቸው። መነሻቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅምን የማስጠበቅ ዓላማን አንግቦ መታገል ሲሆን፥ የመድረሻቸው ማጠየቂያ የተመረኮዘው፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አቸናፊነት ነው። በማነኛውም መስፈሪያ የወያኔ ጊዚያዊ ኃይል ቢለካ፥ ቢመዘን፥ ቢገመገምና ቢተነተን፥ የመጨረሻው አቸናፊ ሆኖ የሚወጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል መሆኑን ያምናሉ። ይህ በሕዝብ ትግል አቸናፊነት ላይ የማያወላውል ዕምነት ያለውና የሀገርን ጥቅም በማስቀደም የሚታገል ኃይል ደግሞ ምንም ምን ቢሆንና የማነኛውንም የውጭ ኃይል ርዳታ በማግኘት ሕዝብን የሚጨቆን አምባገነናዊ ሥርዓት በመጨረሻ በሕዝባዊ ትግል እንደሚንኮታኮት የታሪክ ሀቅ መሆኑን አበክሮ ይረደዋል። ይህም በመሆኑ በትግሉ ሂደትና አድማስ ዕይታ ችንፈትንና ተንበርካኪነትን የሚያይበት የትግል መነፅር አይኖረውም።

እንዲያውም፥

“ ታርሶም ተሸምቶም ይበላል እንጀራ፥
እንዴት አለሽ ጥቃት፥ እንዴት አለሽ ችንፈት
የሞት ባልንጀራ፥
ርሀብን መርጠኩኝ፥ ከዓላማየ ጋራ፥ ከኩራቴ ጋራ

እንዛለሁ እንጅ፥ አርማየን አንግቤ በተሰዉት ጎራ”

የሚለውን እንጉርጉሮ እያዜመ ይቀጥላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የድሉ ባለቤት እስከ ሚሆን ድረስ!

ለእንደዚህ ዓይነቱ ኃይል፥ እንደ ችንፈት የሚቆጥረው፥ ዓላማውን ሽጦ፥ የትግል ዓርማውን ረግጦ፥ የተነሳበትን ምክንያት ረስቶ፥ የራዕይ አቅጣጫውን ስቶ፥ የገባበትን ቃለ-መሃላ ክዶ፥ የሰማዕታቱን ደም አርክሶ፥የጀግንነቱን ዝናር ፈትቶ፥ ሀገሩንና ሕዝቡን ከድቶ፥ ለወያኔ ተንበርክኮና የውርደት ሞትን ተቀብሎ ዘለዓለማዊ ሀፍረትን ተከናንቦ ሲቀር ነው። ይህ ደግሞ ሰማይ ዝቅ መሬት ከፍ ቢል የሚሆን አይደለም።

ታዲያ ችንፈት ሲሉና እኛ ደግሞ ድል ስንል ያለው ልዩነት ይህ ነው። ይህም የጨለማና የብርሃን ያህል ልዩነት አለው። እኛ ለድል እየታገልን ለድል ስንበቃ፥ እነርሱ በችንፈት ሌጦ ታጅለው፡ ወደ ሀፍረት- ጉድጓድ ይገባሉ ።

ኖቬምበር 2007